በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር
The Federal Democrataic Republic Of Ethiopia
Ministry Of Trade & Regional Integration

ቀን/Date ጥቅምት 28 2016

ቁጥር/No 011-30/80/846

ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ

ለኦሮሚያ ንግድ ቢሮ

<u>አዲስ አበባ</u>

ለድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ንግድ፣ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ

<u>ድሬዳዋ</u>

ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ

<u>ባህርዳር</u>

ለሐረሪ ብ/ክ/መንግስት ንግድ፣ኢንዱስትሪና ልማት ቢሮ

<u>ሐረሪ</u>

ለደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል ንግድ ቢሮ

<u>አርባ ምንጭ</u>

ለማዕከላዊ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል ንግድ ቢሮ

<u>ቡታጅራ</u>

ለሲዳማ ብ/ክ/መ/ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ

<u>ሀዋሳ</u>

ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል መንግስት ንግድ ቢሮ

<u>ቦንጋ</u>

ለሶማሌ ብ/ክ/መ/ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ

<u>ጅግጅጋ</u>

ለጋምቤላ ብ/ክ/መ/ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ

<u>ጋምቤላ</u>

ለአፋር ብ/ክ/መንግስት ንግድ፣ኢንዱስትሪና ትራንስፖርት ቢሮ

<u>ሰመራ</u>

ለቤንሻንጉል ጉምዝ ብ/ክ/መ/ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ትራንስፖርት ቢሮ

<u>አሶሳ</u>

ጉዳዩ:- <u>የጫት ላኪነት ንግድ ስራ ፈቃድ ቅድመ ፈቃድ መስፈርትን ስለማሳወቅ</u>

የጫት ወጪ ንግድን በመከታተልና ድጋፍ በመስጠት፣ ያሉበትን ማነቆዎች በመፍታት እና ለሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ግኝት አስተዋፅኦውን ለማሳደግ እንዲቻል የጫት ላኪነት ንግድ ስራ ፈቃድ ያላቸውም ሆነ አዲስ የጫት ላኪነት ንግድ ስራ ፈቃድ ማውጣት የሚፈልጉ ነጋዴዎች ማሟላት ያለባቸውን መስፈርት ከዚህ ደብዳቤ ጋር በተያያዘው ሰርኩላር መሰረት የሚፈጸም መሆኑን እየገለጽኩ ከጥቅምት

ገብረመስቀል ጫላ ሞጣሎ
ሚኒስትር

Tel-251-5518025
Fax-251-5501697
P.O BOX-704
F.B:-
Email:-fdremotri@gmail.com

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa,Ethiopia

# የጫት ላኪነት ንግድ ስራ ፈቃድን በተመለከተ የወጣ የቅድመ ፈቃድ የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት

የጫት ወጪ ንግድ ስራ የአርሶ አደሩን ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ አግባብ መመራት ያለበት በመሆኑ፣ ሀገሪቱ ከጫት ወጪ ንግድ ማግኘት የሚገባትን የውጭ ምንዛሪ እያገኘች ባለመሆኑ ህገወጥ ነጋዴዎችን ከግብይት ስርዓቱ እንዲወጡ በማድረግ ህጋዊ ነጋዴዎችን ማበረታታት አስፈላጊ በመሆኑ እና በውድድር ላይ የተመሰረተ የግብይት ተዋናዮችንና ሀገሪቱን ተጠቃሚ የሚያደርግ የግብይት ስርዓት ማመቻቸት አስፈላጊ በመሆኑ

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ከዚህ የሚከተለውን የጫት ላኪነት ንግድ ስራ ፈቃድ የቅድመ ፈቃድ የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት አውጥቷል።

1. **የጫት ላኪነት ንግድ ስራ የቅድመ ፈቃድ የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት**

ማንኛውም በጫት ላኪነት ንግድ ስራ የተሰማራ ወይም መሰማራት የሚፈልግ ሰው ቀጥሎ የተዘረዘሩትን የጫት ላኪነት ንግድ ስራ ፈቃድ የቅድመ ፈቃድ የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች በሙሉ ማሟላት ይኖርበታል።

1.1 የጫት ምርት ማጓጓዝ የሚችል መሸፈኛ መረብ ያለውና ጂፒኤስ የገጠመ ተሽከርካሪ ለማቅረብ ግዴታ የሚገባ፤

1.2 አዲስ ፈቃድ ጠያቂ ከሆነ በበጀት አመቱ ቢያንስ 100 ሜትሪክ ቶን ጫት ለመላክ ግዴታ የሚገባ ወይም ነባር ባለፈቃድ ከሆነ በተጠናቀቀው የበጀት አመት ቢያንስ 100 ሜትሪክ ቶን ጫት መላኩን ማረጋገጫ የሚያቀርብ ወይም ቢያንስ 500 ሺህ የአሜሪካን ዶላር ገቢ ማስገባቱን ማረጋገጫ የሚያቀርብ ፤

1.3 በሀገር ውስጥ የጫት ንግድ ስራ ላይ በማናቸውም ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የማይሰማራ መሆኑን ግዴታ የሚገባ፤

1.4 በጫት ላኪነት ንግድ ስራ በባንክ የተበላሸ የውጭ ምንዛሪ (Delquent list) ዝርዝር ውስጥ ያልገባ ለመሆኑ ማስረጃ የሚያቀርብ፤እና

1.5 የጫት ምርት ማዘጋጃው

ሀ) ወለሉ እና ግድግዳው ከኮንክሪት የተሰራ

ለ) ስፋቱ ከ100 ካሬ ሜትር ያላነሰ

ሐ) ከፍታው ከ 5 ሜትር ያላነሰ

መ) በቀላሉ አየር ማስገባት የሚችል መስኮት ያለው የራሱ መጋዘን ለመሆኑ የይዞታ ማረጋገጫ የሚያቀርብ ወይም ከላይ በፊደል ተራ ሀ እስከ መ የተዘረዘሩትን የሚገልጽ አግባብነት ባለው የውል አዋዋይ ባለስልጣን የተረጋገጠ የኪራይ ውል የሚያቀርብ መሆን አለበት።

2. **የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለማውጣትና የንግድ ስራ ፈቃድ ስለማደስ**

ቀደም ሲል የንግድ ስራ ፈቃድ ያወጣ ወይም ያደሰ ማንኛውም የጫት ላኪነት የንግድ ስራ ፈቃድ ያለው ነጋዴ ከጥቅምት 27 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ህዳር 15 ቀን 2016 ዓ.ም. ድረስ ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በግንባር ቀርቦ የተጠየቁትን መስፈርቶች በማሟላት የቅድመ ፈቃድ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማውጣትና የንግድ ስራ ፈቃዱን ማደስ ይኖርበታል ።

3. ስለተፈፃሚነት

ይህ የቅድመ ፈቃድ የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት ከጥቅምት 27 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

ጥቅምት 27 ቀን 2016 ዓ.ም.

ገብረመስቀል ጫላ ሞጣሎ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚኒስትር

28 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ አዲስ በሚሰጣቸዉ ወይም በሚታደስላቸዉ ንግድ ስራ ፍቃድ ብቻ አገልግሎት የሚያገኙ መሆኑን አስታዉቃለሁ።

ከሰላምታ ጋር

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር Ministry of Trade and Regional integration

ገብረመስቀል ጫላ ሞጣሎ
ሚኒስትር

እንዲያውቁት፣

- ለክቡር የንግድ ትስስርና ወጪ ንግድ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ
- ለክቡር የንግድ ስርዓትና ላይሰንሲንግ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ
- ለክቡር የጥራትና ማረጋገጫ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ

ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር

ግልባጭ፡-

- ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለፌደራል ጉምሩክ ኮሚሽን
- ለፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን
- ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ
- ለፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት

አዲስ አበባ